የተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን



የኪስ ማስታወሻ

መስከረም 2014 ዓ.ም.



የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን

የተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ

የኪስ ማስታወሻ

መስከረም 2014 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

የተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የአካባቢ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን

የኪስ ማስታወሻ 2014 ዓ.ም.

1. መግቢያ

ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሏትን በርካታ ተግባራት በማከናወን ላይ ትገኛለች። በዚህም ከሀገራዊ ፋይዳው ባለፈ ዓለማቀፋዊ እውቅና ያስገኘላትን ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂን በ2003 ዓ.ም ይፋ አድርጋለች። በዓለም አቀፍ ደረጃም የሚጠበቅባትን ሀላፊነት ለመወጣት አንዱ አካል የሆነውን በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሀገራዊ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ያዘጋጀችና ለተ.መ.ድ. የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት ሴክሬቴሪያት በ2007 ዓ.ም. ያስገባች ሲሆን ይህንኑ ዕቅድ የፓሪሱ ስምምነት በሚያስቀምጠው ድንጋጌ መሰረት ተሻሽሎ በድጋሚ በሐምሌ 2013 ዓ.ም. ለሴክሬቴሪያቱ አስገብታለች።

የተሻሻለውን የኢትዮጵያን በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ አጠቃላይ ይዘት ለአንባቢያን በቀላሉ ተደራሽ ለማድረግ እና እንዲገነዘቡ ለማስቻል ታስቦ ይህ የኪስ ማስታወሻ ተዘጋጅቷል። በሰነዱም በሀገራችን የአየር ንብረት ለውጥ በማድረስ ላይ ያለው ተፅዕኖና እየተወሰዱ ያሉ ስትራቴጂያዊ እርምጃዎች፣ የክለሳ ሂደት፣ በቀጣይ 10 ዓመታት ሀገራችን ቅድሚያ ሰጥታ የምትተገብራቸው ዋና ዋና የስርየትና የማጣጣሚያ ተግባራት፣ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጫ ማዕቀፎችና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት፣ ለትግበራ የሚያስፈልጉ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የአቅም ግንባታ ግብዓት ፍላጎቶች እንዲሁም የካርቦን ግብይት ተሳትፎ ተካተዋል።

1.2 የተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ምንነት

የተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ የሚሸፍነው ከ2013 - 2022 ዓ.ም ሲሆን በመጀመሪያው ዕቅድ ላይ የተደረገውን ማሻሻያም በዝርዝር ያመላክታል።

የማሻሻያ ሂደቱ ሀገራዊ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ለመስጠት የወጡና በትግበራ ላይ የዋሉ ፖሊሲዎች መሰረት ያደረገ ሲሆን የመጀመሪያው በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ፣ ሀገራዊ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ እቅድ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስልት የአፈፃፀም ግምገማ፣ የአረንጓዴ አሻራ ትግበራ እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂን እንደ ዋነኛ ምሶሶ ያስቀመጠው የሀገሪቱ የ10 ዓመታት የልማት ዕቅድ በዋናነት ይጠቀሳሉ። በማሻሻያው ሂደትም ሁሉን አቀፍ በሆነ መልኩ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የተቀናጀ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ሞዴልን (Green Economy Model) በመጠቀም አጠቃላይ የማህበራዊ ኢኮኖሚ ትንተናም ተከናውኗል። በዚህም ሀገራዊ የኢኮኖሚ ዕድገትና የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መረጃዎች በመከለሳቸው በዕቅድ ትግበራ ዘመኑ የሚኖረው የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትና ቅነሳ ትንበያ በፊት ከነበረው የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀትና ቅነሳ መጠንን ያሻሻለ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ከሀገር ውስጥ በሚመደብ እና ከአጋር አካላት በሚገኝ ሀብት

የሚተገበሩ የስርየትና የማጣጣሚያ ተግባራት በሰነዱ ውስጥ በግልፅ ተለይተው ተካተዋል።

በዚህም መሰረት ኢትዮጵያ በ2013 ዓ.ም ታህሳስ ወር ላይ ለተባበሩት መንግሰታት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት ካስገባችው ረቂቅ ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር በሐምሌ 2013 ዓ.ም. የገባው ዕቅድ የተወሰኑ ለውጦች አካቷል። ይህንን የማሻሻል ሂደት መከተል ያስፈለገበት ምክንያት የተከለሰው ዕቅድ ከሀገሪቱ የልማት ዕቅድ ማዕቀፍና ፖሊሲ ጋር ሙሉ በሙሉ የተጣጣመ እንዲሆን ለማስቻል ነው። ውጤቱንም በተለያዩ ወቅቶች በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የመገምገምና የማሻሻል ስራ ተከናውኗል። ዕቅዱንም በማዘጋጀት ሂድት ውስጥ የሚከተሉት ወሰኝ ተግባራት ተከናውነዋል፤

የማስተሰሪያ አስተዋፅኦን በተመለከተ፣

1. በተለመደው አሰራር (BAU) የሚለቀቀውን የሙቀት አማቂ ጋዝ የልቀት መጠን የመከለስ፤
2. የማስተሰረያ ድርጊቶች በመተግበር እስከ 2022 ዓ.ም የሚኖረውን የልቀት ቅነሳ መጠን የማስላት፤
3. የ2017 እና የ2022 ዓ.ም የልቀት ቅነሳ ሚላማዎችን የማስቀመጥ፤
4. የማስተሰረያ ተግባራትን አፈፃፀም ለመለካት የሚያስችሉ አመላካቾችን የመለየት፤
5. በሀገር ሀብትና ከአጋር አካላት በሚገኝ ድጋፍ የሚተገበሩ የፖሊሲ አማራጮችን እና የኢትጵያን የካርቦን ግብይት ተሳትፎ ማሳድግ የሚያስችሉ ተግባራትን የመለየት ስራዎች ተከናውነዋል።

የአየር ንብረት ለውጥ የማጣጣሚያ አስተዋፅኦዎችን ለመለየት የማጣጣሚያ ፖሊሲዎችና ስልቶችን፤ የ2010 ዓ.ም. መነሻ መረጃ (baseline data) እና የ2022 ዒላማዎችን እንዲሁም 40 የማጣጣሚያ ተግባራትን ከነአመላካቾቻቸው የማስቀመጥ ስራ ተከናውኗል። በተጨማሪም የተሻሻለ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጫ እና የክትትልና ግምገማ ስርዐት የትግበራ ዕቅድ ተካቷል።

2. ሀገራዊ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖና ተጋላጭነት

ኢትዮጵያ ለዓለም አቀፍ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ያላት ድርሻ ዝቅተኛ ሲሆን ይህም 0.04 በመቶ ይገመታል። ነገር ግን ሀገሪቱ ለአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖዎች በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ ከሆኑ ሀገራት አንዷ ናት። ይህም ሊሆን የቻለበት ዋንኛው ምክንያት በዝናብ እና በተፈጥሮ ሀብት ላይ ጥገኛ የሆነ ኢኮኖሚ ያላት በመሆኑና የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን የመቋቋም አቅሟም አነስተኛ በመሆኑ ነው። ከ1952 ወዲህ የሙቀት መጠን በአማካይ በ1 ዲግሪ ሴልሺየስ መጨመሩን ጥናቶች ያመለክታሉ።የዝናብ መጠን ተለዋዋጭነት በዓመት ውስጥ የሚታየው ልዩነት በአማካይ 25% የሚገመት ሲሆን በአንዳንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ 50% ይደርሳል። ይህ እንዳለ ሆኖ ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት የሀገሪቱ የደቡብ ማዕከላዊ አካባቢ የዝናብ መጠን በ20% የመቀነስ አዝማሚያ አሳይቷል። ከባለፉት 10 ዓመታት ወዲህም እንደ ድርቅና ጎርፍ የመሳሰሉ የአየር ንብረት ለውጥ አስከፊ ክስተቶች በተደጋጋሚ መመልከት የተለመደ ሆኗል። በተጨባጭ ደግሞ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖና ተጋላጭነት በሁሉም ዘርፎችና የሀገሪቱ ክፍሎች በተለያየ ደረጃ እየተከሰተ ይገኛል።

2.1. የፖሊሲ፣ የህግና መዋቅራዊ ማዕቀፍ

የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት ከፀደቀበት ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ የመስጠት ሥራ እያደገ መጥቷል።

ሀገራችን ለተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት የመጀመሪያውን ሀገራዊ የኮሚኒኬሽን ሰነድ በ1993 ዓ.ም፣ ሁለተኛውን በ2007 ዓ.ም ያስገባች ሲሆን በ1999 ዓ.ም ደግሞ ሀገራዊ የማጣጣሚያ ፕሮግራም (NAPA)፣ እንደዚሁም በ2002 ዓ.ም የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ፕሮግራምንና (EPACC) አግባብነት ያለው ሀገራዊ የማስተሰሪያ ተግባራትን (NAMA) ይፋ አድርጋለች።

ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይገበር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት በ2002 ዓ.ም ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጅን አዘጋጅታለች። ከዚህ ውጪ ዘርፍ ተኮር ስትራቴጂያዊ ትግበራን ለማሳለጥ የዘርፍ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ፖሊሲና ስትራቴጂዎችም ተነድፈዋል። የግብርና እና ደን (2007 ዓ.ም) ፣ የውሃ መስኖና ኢነርጂ (2007 ዓ.ም) ፣ የትራንስፖርት (2007 ዓ.ም)፣ ሀገራዊ የጤና (2009 ዓ.ም) ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ስትራቴጂዎች ተዘጋጅተዋል። በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድን በ2007 ዓ.ም ለተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት ሴክሬተሪያት አስገብታለች። ይህ የመጀመሪያው እቅድ ከተለመደው አሠራር ጋር ሲነፃፀር ከሁሉም ዘርፎች ሊለቀቅ ይችል የነበረውን የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት መጠን በ2022 ዓ.ም በ64% ለመቀነስ ያለመ ነበር።


የአየር ንብረት ተፅዕኖን ለመቋቋም በሚደረግ ጥረት ሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድን (NAP-ETH) በ2009 ዓ.ም ተዘጋጅቷል። የትግበራ ሂደቱን የሚያግዙ የስርዐተ ፆታ ትንተና ሰነድ፣ የትግበራ ፍኖተ-ካርታና የሀብት ማፈላለጊያ ስትራቴጂዎችም ተዘጋጅተዋል።

ሀገራችን የአየር ንብረት ለውጥ ፖሊሲና ስትራቴጂን በልማት ዕቅዶቿ ውስጥ በማካተት ስትተገብር ቆይታለች። በዚህም መሰረት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስትራቴጂን በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ በማካተት ተተግብሯል። በቅርቡ የፀደቀው የ10 ዓመት የልማት ዕቅድም ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባትን እንደአንድ ስትራቴጂ ምሰሶ አስቀምጧል።

ባለፉት የእቅድ ትግበራ ዓመታት ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመተግበር በሂደት እያደገ የመጣ ዘርፍ ተኮር መዋቅራዊ አሰራር ተዘርግቷል። በዚህም የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖዎች ምላሾችን በሀገር አቀፍ ደረጃ በማስተባበር አፈፃፀሙን የሚያግዙ የተለያዩ የአካባቢ ህጎችና ስታንዳርዶች እያወጣና የዘርፎችን የፕሮግራምና የዕቅድ ትግበራዎችን በመምራት ላይ ይገኛል። መዋቅራዊ አደረጃጀቱ ዘርፍ ተኮርና ባለ ብዙ ዘርፍ ሂደትን የተከተለ ሲሆን ሂደቱን በበላይነት የሚከታተሉ የሚኒስትሮች እና የማኔጅመንት ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል። አዛኛዎቹ ሚኒስቴር መ/ቤቶች የስራውን ትግበራ በመደበኛነት የሚከታተሉ ክፍሎችም አደራጅተዋል።

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት መተግበሪያ ፋሲሊቲ በ2005 ዓ.ም የተቋቋመ ሲሆን ፋሲሊቲውም ለስልቱ ትግበራ የሚረዱ ፋይናንስ ነክ ጉዳዮች ላይ የማስተባበርና የመምራት ተግባርን ያከናውናል። በተጨማሪም የቴክኒክ ጉዳዮችና ለትግበራው የሚረዱ መመሪያዎች የማውጣት ሚና ይጫወታል።

የሚከተለው ምስል ከ1986 ዓ.ም ያለውን የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ፖሊሲ ፍኖተ-ካርታ ይዘረዝራል።



ምስል 1- የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ፖሊሲ ፍኖተ-ካርታ

3. በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ የማሻሻያ ሂደት

3.1. የማሻሻያው ሂደት

ሀገራዊ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ የማሻሻያ ሂደት ሰፊ የሰነድ ግምገማ በማካሔድ፣ ተጨማሪ መረጃ በመሰብሰብ፣ መልካም ተሞክሮዎችን እና የባለድርሻ አካላት ምክክርን በማድረግ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ከዚህ በተጨማሪም የሙቀት አማቂ ጋዞች የልቀት ትንበያ ሂደት የመንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ አሰራር መመሪያን (IPCC-2006) መሰረት ያደረገ ነው።

የዕቅዱ የማጣጣሚያ ክፍል ቀደም ብሎ ስራ ላይ የነበረውን የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ የማጣጣሚያ ዕቅድና የዕቅዱን የማስተግበሪያ ፍኖተ ካርታ እና የሀብት ማፈላለጊያ ስትራቴጂ፣ የተለያዩ ዘርፎችን የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነት የግምገማ ሰነድ እና የሌሎች ነባርና ጠቃሚ ሰነዶች ግምገማ ላይ በመመስረት የተዘጋጀ ነው። ከዚህም ባሻገር በረዥም ጊዜ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የሚተገበሩ ተግባራትም ተለይተዋል። በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተው የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅዱን ለማሳካት የሚያስፈልገው የፋይናንስ ፍላጎት ትንበያ የሀገሪቱን የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ ግቦችና ዒላማዎችን ታሳቢ በማድረግ ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም የተሻሻለውን በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተው የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድን ሊደግፍ በሚችል አግባብ ዝርዝር የሥርዓተ-ፆታ ትንተና እና የተቋማት የአቅም ክፍተት ትንተናዎች ተካሂደዋል።

3.2 ፍትሃዊነት እና ፍላጎት (faireness and ambition)

የተሻሻለው በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ መሻሻልን የሚያመላክቱ ማሳያዎች፣


1	የሙቀት አማቂ ጋዞችን የልቀት አማራጮች(pathways) በጥልቀት በማጤን ልቀቶችን ለመቀነስ በተቀመጡ ዒላማዎችና የአሠራር ማሻሻያዎች አማካይነት፣በሀገር አቀፍ ደረጃ የተለቀቁ የሙቀት አማቂ ጋዞች ክምችትን በውል በመለየት፣ታሪካዊ ልቀቶችን እና የልቀት አማራጮችን በበለጠና በትክክል እንዲሁም አጠቃሎ በመያዝና ከብሄራዊ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልኬት እና ከተሻሻሉ የልቀት መጠን መለኪያዎች (emission factorስ) ጋር በማጣጣም፣ እንዲሁም ከበይነ መንግስታት የሙቀት አማቂ ጋዞች የልኬት መመሪያ (IPCC 2006) ጋር የተሻለ ወጥነትን መፍጠሩ፤
2	በዕቅዱ ኢትዮጵያ የ68.8% የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን የመቀነስ ግብ ያስቀመጠች መሆኑ፤
3	በመጀመሪያው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተው የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ላይ ያልታዩ ዝርዝር የማጣጣሚያ እርምጃዎች መነሻ እና የ2022 ዓ.ም ዒላማዎች መካተታቸው፤
4	በሀገር ውስጥ ሀብትና በለጋሽ ሀገራት ድጋፍ የሚተገበሩ የማስተሰርያና የማጣጣሚያ ስራዎች በግልፅ ተለይተው መቀመጣቸው እና ከመጀመሪያው ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር ትርጉም ያለው የሀገር ውስጥ ሀብት መታቀዱ፤

5	ተጨማሪና አዳዲስ እርምጃዎች በዕቅዱ ውስጥ ለማካተት ምቹ ሁኔታዎች መፈጠራቸው፤
6	በየዘርፉ ተጨማሪ የማጣጣሚያ እርምጃዎች መካተታቸው፤
7	በዕቅዱ ውስጥ ያልታዩና ለወደፊቱ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ያልተጠበቁ የፖሊሲ ለውጦች ሊከሰቱ ቢችሉ ይህ ዕቅድ በሚፈጠረው ለውጥ ማዕቀፍ ውስጥ ተጣጥመመውና ተላምደው ሊያሰሩ የሚችሉ የአሠራር ስልቶችን መቀየሱ፤ እና
8	የተሻለ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትና ቅነሳ የልኬት፣ የዘገባና የማረጋገጥ እንዲሁም ጥብቅ የትግበራ ክትትል እና ግምገማ በማድረግ የማስተሠርያና የማጣጣሚያ እርምጃዎች ያመጡትን ለውጥ መለየት እንዲቻል ሆኖ መዘጋጀቱ የሚሉት ነጥቦች ናቸው።

3.3. የእቅዱ የአተገባበር ሁኔታ

በተሻሻለው በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ውስጥ ከተካተቱት አበይት ጉዳዮች መካከል ዕቅዱን ተግባራዊ ለማድረግና ለማሳካት በሀገር ውስጥ በሚመደብ ሀብትና በለጋሽ ሀገራት ትግበራ የሚሳኩ ዒላማዎችን በግልፅ ለይቶ ማስቀመጥ መቻሉ አንዱ እርምጃ ነው። በዚህም ተሻሽሎ በተዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ የተቀመጡት የፖሊሲ ትግበራዎችና ዘርፈ ብዙ የፕሮግራም ድርጊቶች ሲሆኑ ለትግበራቸውም የአገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ የሀብትና የቴክኒክ ድጋፍ አቅርቦቶችን ይፈልጋሉ። ከሌሎች አገሮች ልምድ እና ከሀገራዊ ኢኮኖሚያዊ

ተጨባጭ እውነታዎች በመነሳት ሀገሪቱ ከጠቅላላው የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ዒላማዋ 20% በሀገር ውስጥ ፋይናንስ የሚፈፀም ሲሆን ቀሪው 80% ደግሞ በዓለም አቀፍ ድጋፍ የሚገኝ መሆኑ ተመላክቷል። ይህም የሆነበት ምክንያት ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ግዴታ የሚጥልባት ታሪካዊም ሆነ የአሠራር ስርዐት ባለመኖሩ፣ ሀገሪቱ በዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ የምትገኝ መሆኗና የአገር ውስጥ ሀብት ውሱንነት መኖር እና ሀገሪቱ ባላት ውስን ሀብት ሌሎች ዘላቂ የልማት ስራዎችን ቅድሚያ መሥጠቷን ከግምት ውስጥ ያስገባች በመሆኑ ነው። በተጨማሪም የሀብት ክፍፍሉ ኢትዮጵያ ዝቅተኛ ወጪ ያላቸውን የማስተሰርያ ተግባራትን ቅድሚያ ሰጥታ እንደምትተገብር ታሳቢ አድርጓል።




ምስል 2 – ከሀገር ውስጥ ሀብትና ከለጋሽ ሀገራት ድጋፍ የሚገኝ የፋይናንስ ምንጭ

4. ኢትዮጵያ ለሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ያላት አስተዋፅኦ


4.1. በተለመደው አሰራር ሊኖር የሚችል የልቀት መጠንን ለመቀነስ በሀገር ውስጥ ሀብትና በለጋሽ ሀገራት ድጋፍ የሚከናወኑ ተግባራት

በመጀመሪያው የሀገራችን በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ የነበረው በተለመደው አሰራር የሚኖረው የመነሻ ዓመት የልቀት መጠን፤ ከተሻሻለው ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ልዩነት ያለው ሲሆን ይህም የሆነበት ምክንያት ማሻሻያው ጥቅም ላይ ባዋላቸው አዳዲስ ዘዴዎችና መረጃዎች ምክንያት ነው። በዚህም የተሻሻለው የመነሻ ዓመት (2002 ዓ.ም) የልቀት መጠን 247 ሚ.ሜ.ቶን ካርቦንዳይኦክሳይድ እኩሌታ ሲሆን ይህም በተለመደው አሰራር በ2022 ዓ.ም የልቀት መጠኑ 403.5 ሚ.ሜ.ቶን እንደሚደርስ ተተንብዮአል። ትንበያው በሶስት መንገዶች ማለትም በሀገር ውስጥና በለጋሽ ሀገራት ከሚገኝ ሀብት ትግበራ የሚገኝ የልቀት ቅነሳና በተለመደው አሰራር የሚኖር ልቀት ቅነሳ በሚል ይከፈላል። በሀገር ውስጥ በሚመደብ ሀብት በሚተገበሩ የማስተሰሪያ ስራዎች በ2022 ዓ.ም የ347 ሚ.ሜ.ቶን የልቀት መጠን ሲኖር ይህም ከተለመደው የ14% ወይንም የ56 ሚ.ሜ.ቶን ልቀት ቅነሳ ያሳያል። በለጋሽ አካላት ድጋፍ ደግሞ በ2022 ዓ.ም የሚኖረው የልቀት መጠን 125.8 ሚ.ሜ.ቶን የካርቦንዳይኦክሳይድ እኩሌታ ይሆናል። ይህም ከተለመደው አሰራር ጋር ሲነፃፀር አጠቃላይ የልቀት ቅነሳው የ68.8% ወይንም የ277.7 ሚ.ሜ.ቶን መሆኑን ያሳያል (ምስል 3ን ይመልከቱ)። ይህ የተለጠጠ ዕቅድ

የሚከናወነው በሀገር ውስጥ ሀብት ትግበራ የሚገኘውን የልቀት ቅነሳም ያካትታል።



*ምስል 3- የተከለሰው በተለመደው አሰራር የሚኖር ልቀት፣ በሀገር ውስጥ ሀብትና በለጋሽ ሀገራት ድጋፍ የሚከናወኑ ተግባራት*ከዚህ በታች ያለው ምስል ዘርፎች ለልቀት ቅነሳው ያላቸውን ደርሻ በንፅፅር ያስቀምጣል።



ምስል 4- ሀገራዊ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትና ቅነሳ በዘርፍ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በቀጣይ ዓመታት ውስጥ በመዋቅራዊ የለውጥ ሂደት ውስጥ እንደሚያልፍ ይጠበቃል። የ10 ዓመቱ የልማት ዕቅድም የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የአምራች ዘርፍ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም ከፍተኛ የሆነ የከተሞች መስፋፋት ይኖራል። እነዚህ ሁኔታዎች የልቀት መጠኑ ላይ የራሳቸው የሆነ ድምር ተፅዕኖ ይኖራቸዋል። የግብርናው ዘርፍ በተለይም የእንስሳት ዘርፉ በቀጣይ ዓመታት ለሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ዋነኛ ድርሻ ሊኖረው እንደሚችል የሚገመት ሲሆን ከሱ በመከተል ደግሞ የመሬት አጠቃቀም ለውጥና የደን ዘርፍ በርካታ ልቀት እንደሚኖረው ይታመናል። እነዚህ ዘርፎች በ2022 ዓ.ም በተለመደው አሰራር ለሚኖው የልቀት መጠን የ83% ድርሻ (የመሬት አጠቃቀም ለውጥና ደን ዘርፍ 35% እና የእንሰሳት 48%) ይኖራቸዋል።

ቀጥሎ ያለው ሰንጠረዥ (ሰንጠረዥ 1) ዘርፎች ከሀገር ውስጥ በሚመደብና ከለጋሽ ሀገራት በሚገኝ ሀብት ለሚኖረው የልቀት ቅነሳ ያላቸውን ድርሻ ያሳያል።

ሰንጠረዥ 1- በተለመደው አሰራር የሚኖር ልቀት ትንበያ፣ በሀገር ውስጥ ሀብትና በለጋሽ ሀገራት ድጋፍ ከሚከናወኑ ተግባራት የሚገኝ የልቀት ቅነሳ

ዘርፍ	በተለመደው አሰራር የሚኖረው ልቀት መጠን ትንበያ (ሚ.ሜ.ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ)			በሀገር ውስጥ በሚመደብ ሀብት ትግበራ የሚኖረው የልቀት መጠን (ሚ.ሜ.ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ)		ከለጋሽ ሀገራት በሚገኝ ሀብት ትግበራ የሚኖረው የልቀት መጠን (ሚ.ሜ.ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ)	
	2020	**2025**	**2030**	**2025**	**2030**	**2025**	**2030**
ኢንዱስትሪ	5.9	12.7	26.1	12.9	27.3	10.2	22.6
ኢነርጂ	10.7	14.4	20.0	12.7	14.9	10.4	9.5
የመሬት አጠቃቀም ለውጥና ደን ዘርፍ	125.0	133.8	140.2	112.6	91.8	21.4	-99.9
እንሰሳት	146.4	169.5	194.8	168.7	192.9	162.8	180.0
ሰብል	5.8	8.1	11.0	8.0	10.9	8.0	10.6
ቆሻሻ	9.1	10.3	11.5	9.4	9.5	6.0	2.9
አጠቃላይ (ሚ.ሜ.ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ)	**302.9**	**348.8**	**403.5**	**324.3**	**347.3**	**218.8**	**125.8**

የዘርፎች የልቀት ቅነሳ አቅም በሚከተለው ሰንጠረዥ 2 ተመላክቷል።

ሰንጠረዥ 2- በተለመደው አሰራር የሚኖረው የልቀት መጠን እና በሀገር ውስጥና ከለጋሾች በሚገኝ ሀብት የሚገኝ የልቀት ቅነሳ

ዘርፍ	በተለመደው አሰራር የሚኖረው ልቀት መጠን ትንበያ (ሚ.ሜ.ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ)		በሀገር ውስጥ በሚመደብ ሀብት ትግበራ የሚኖረው የልቀት ቅነሳ (ሚ.ሜ.ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ)		ከለጋሽ ሀገራት በሚገኝ ሀብትና በሀገር ውስጥ በሚመደብ ሀብት ትግበራ የሚኖረው የልቀት ቅነሳ (ሚ.ሜ.ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ)	
	2025	**2030**	**2025**	**2030**	**2025**	**2030**
ኢንዱስትሪ	12.7	26.1	-0.2	-1.2	2.5	3.5
ኢነርጂ	14.4	20.0	1.7	5.1	4.0	10.5
የመሬት አጠቃቀም ለውጥና ደን ዘርፍ	133.8	140.2	21.2	48.4	112.3	240.1
እንሰሳት	169.5	194.8	0.8	1.8	6.7	14.8
ሰብል	8.1	11.0	0.0	0.1	0.1	0.3
ቆሻሻ	10.3	11.5	0.9	2.0	4.3	8.6
አጠቃላይ (ሚ.ሜ.ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ)	**348.8**	**403.5**	**24.5**	**56.2**	**129.9**	**277.7**

በሚቀጥለው ክፍል የዘርፍ ልቀትና የስርየት ተግባራት በዝርዝር ይቀርባሉ። ከለጋሽ ሀገራት በሚገኝ ሀብት ትግበራ የልቀት ቅነሳ ዒላማ በሀገር ውስጥ በሚመደብ ሀብት ትግበራ የሚኖረው የልቀት ቅነሳ ያጠቃልላል።

4.2. የመሬት አጠቃቀም ለውጥና ደን ዘርፍ

ከመሬት አጠቃቀም ለውጥና ደን ዘርፍ የሚወጣው የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ምንጩ ከመሬት አጠቃቀም ለውጥና የባዮማስ ኢነርጂን ከመጠቀም ነው። የደን መሬትን እንደ አንድ ብቸኛ የመሬት ክፍል ከሚያየው ከመጀመሪያው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ በተቃራኒ የዚህ ዘርፍ የካርቦን ክምችት የሚወሰነው እንደ የደን መሬት፣ ረግረጋማ መሬት፣ የእርሻ መሬት፣ የሰፈራና ከሌሎች መሬት አጠቃቀሞች ተለዋዋጭ ባህሪያት የሚመጣ ነው። የትንበያ ውጤቶች እንደሚያሳዩት የመሬት አጠቃቀም ለውጥና ደን ዘርፍ በደን መልሶ ማልማትና ማገገም ሂላማዎች ምክንያት ከፍተኛ የልቀት ቅነሳ አቅም አለው። በተመሰሳይም በተለመደው አሰራር ከሚወጣው ልቀት የመሬት አጠቃቀም ለውጥና ደን ዘርፍ ከጠቅላላ የልቀት መጠን ሁለተኛ ደረጃ ይይዛል። የዘርፉ ፖሊሲ ትግበራዎች በ2022 ዓ.ም የሚኖረውን የልቀት መጠን ወደ -99.9 ሚ.ሜ.ቶን የሚቀንሰው ሲሆን ይህም ዘርፉን ካርቦን የሚከማችበት ዋነኛ ቦታ ያደርገዋል። ይህም በተለመደው አሰራር በ2022 ዓ.ም ከሚኖረው ልቀት ጋር ሲነፃፀር የ171% (-240.1 ሚ.ሜ.ቶን) ልቀት ቅነሳ አለው። በሀገር ውስጥ የሚመደብ ሀብት ትግበራ ደግሞ ልቀቱን ወደ 91.8 ሚ.ሜ.ቶን የሚያደርሰው ሲሆን ይህም ማለት በተለመደው አሰራር በ2022 ዓ.ም ከሚኖረው ልቀት ጋር ሲነፃፀር የ34.6% (-48.4 ሚ.ሜ.ቶን) ቅነሳ ነው።

በኢትዮጵያ የደን ዘርፍ ልማት ዕቅድ መሠረት የአረንጓዴ አሻራ ተግባራትና በREDD+ የስትራቴጂክ የድርጊት መርሐ-ግብር መሰረት ከመሬት አጠቃቀም ለውጥና ደን ዘርፍ የተጣራ የልቀት መጠን ውስጥ ለማግለል የሚቻለው በዘርፉ ወደ 15 ሚሊዮን ሄክታር በሚሸፍነው የደን መልሶ ማልማትና ማገገም የረጅም ዘመን የደን ዘርፍ ግብን ማሳካት ሲቻል ነው።

ይህንን የተለጠጠ ዕቅድ ለማሳካት የሀገሪቱን የደን ሽፋን ወደ 30% ሽፋን እንዲጨምር ያደርገዋል። ከዚህ ዘርፍ ለሚወጣው ልቀት ሌላኛው ምንጩ የባዮማስ ኢነርጂን ለምግብ ማብሰያነት መጠቀም ሲሆን ይህም በዓለም አቀፉ የደን ቆጠራ መመሪያ መሰረት የሚሰላው በዚህ ዘርፍ ውስጥ ነው። ስለዚህ የባዮማስ ኢነርጂን ለምግብ ማብሰያነት መጠቀምን በሌላ አማራጭ የሀይል ምንጮች መተካት ወይም የተሻሻለ ባዮማስን ለሀይል አማራጭነት መጠቀም በደን ላይ ያለውን ጫና እንዲቀንስ ያደርጋል።

4.3. የእንሰሳት ዘርፍ

በሀገራችን የእንስሳት ሀብት ዘርፍ በሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ሁለተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ከዚህም በተጨማሪ በ2002 ዓ.ም መነሻ ዓመት ዘርፉ 45% የልቀት ድርሻ የነበረው ሲሆን በተለመደው አሰራር ከተሄደ በ2022 ዓ.ም ሊኖር ከሚችለው አጠቃላይ ሀገራዊ ልቀት ደግሞ ግማሹን ድርሻ ይይዛል። ዘርፉ ለኢኮኖሚው ካለው ጠቀሜታ በመነሳት የዘርፉን ሀገራዊ የኢኮኖሚ ድርሻ ለማስፋፋት የታሰበ ሲሆን የእንስሳት እርባታን በማሻሻል የልቀት ቅነሳውን ማሳካት ይቻላል። በመሆኑም ከለጋሽ ሀገራት በሚገኝ ሀብትና በሀገር ውስጥ ከሚመደብ ሀብት ትግበራ በዘርፉ የሚወሰዱ የፖሊሲ ትግበራዎች የልቀት ደረጃውን በ2022 ዓ.ም ወደ 180 ሚ.ሜ.ቶን እንዲደርስ ያስችላል።

በሀገሪቱ ያለው አዲስ የእንሰሳት ቁጥር ግምት እና የተከለሰው የልቀት ብዜት (factor) ጥቅም ላይ በመዋላቸው፣ ከመጀመሪያው በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ጋር ሲነፃፀር በተለመደው አሰራር የሚኖረውን የልቀት መጠን እንዲጨምር አድርገውታል። ይህም ማለት ዘርፉ በተለመደው አሰራር በ2022 ዓ.ም

ከሚኖረው ልቀት ጋር ሲነፃፀር የ7.6% (-14.8) ሚ.ሜ.ቶን ልቀት ቅነሳ አቅም አለው። ከሀገር ውስጥ ሀብት በሚገኝ ትግበራ ደግሞ የልቀት መጠኑን ወደ 193 ሚ.ሜ. ቶን እንዲቀንስ ሲያደርገው ይህም በተለመደው አሰራር በ2022 ዓ.ም ከሚኖረው ልቀት ጋር ሲነፃፀር ቅነሳው የ0.92% ነው::

4.4. የኢነርጂ ዘርፍ

በዕቅዱ የሀይል አቅርቦት ዘርፍ የእንሰሳትና የመሬት አጠቃቀም ለውጥና ደን ዘርፎችን በመከተል ከፍተኛ የልቀት ቅነሳን ይዟል። በዋና መስመር ከሚገናኙ የሀይል መስመሮች ከፍተኛ የሀይል ምንጭ የሚገኘው ከታዳሽ ሀይል ነው። የሀይል ዘርፉ በ2022 ዓ.ም ከሚኖረው ልቀት የ5% ድርሻ አለው። በዚህ ዘርፍ ውስጥ የፖሊሲ ትግበራዎች በለጋሽ ሀገራትና በሀገር ውስጥ በሚመደብ ሀብት ትግበራ አማካኝነት በ2022 ዓ.ም የልቀት መጠኑን 9.5 ሚ.ሜ.ቶን እንዲደርስ ያደርጉታል። ይህ ማለት በ2022 ዓ.ም በተለመደው አሰራር ከሚኖረው ልቀት ጋር ሲነፃፀር 52.5% (-10.5 ሚ.ሜ.ቶን) የሙቀት አማቂ ጋዞች ቅነሳ ይኖረዋል ማለት ነው። በሀገር ሀብት በሚመደብ ትግበራ ደግሞ የልቀት መጠኑን ወደ 15 ሚ.ሜ.ቶን ደረጃ እንደሚቀንስ የሚያሳይ ሲሆን በተለመደው አሰራር በ2022 ዓ.ም ከሚኖረው ልቀት የ25.5% ቅነሳ (-5.1 ሚ.ሜ.ቶን) ይኖረዋል። በሀይል ዘርፍ የተቀመጡት የፖሊሲ ተግባራት በሁሉም ዘርፍ ጠቀሜታ ላይ የሚውለውን የሀይል መጠን ይይዛል።

4.5. የቆሻሻ ዘርፍ

ይህ ዘርፍ ዋነኛ የልቀት ምንጭ ከሚባሉት መካከል የሚመደብ ሲሆን እነዚህም ከከተማ የሚወጣ የደረቅ ቆሻሻ፣ የኦርጋኒክ ብስባሽና የደረቅ ቆሻሻን ከማቃጠል የሚመጣ ነው። የማስተሰሪያ ተግባራት ከዚህ ዘርፍ የሚወጣውን ልቀት መጠን ለመቀነስ ከፍተኛ አቅም አላቸው። ዘርፉ በተለመደው አሰራር በ2022 ዓ.ም ለሚኖረው አጠቃላይ ሀገራዊ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት የ3% ድርሻ አለው። በለጋሽ ሀገራትና በሀገር ውስጥ ሀብት ትግበራ በ2022 ዓ.ም የልቀት መጠኑን 2.9 ሚ.ሜ.ቶን ሲያደርሰው ይህም በተለመደው አሰራር በ2022 ዓ.ም ከሚኖረው ልቀት ጋር ሲነፃፀር የ74.7% ቅነሳ (-8.6 ሚ.ሜ.ቶን) ይኖረዋል። በሀገር ውስጥ በሚመደብ ሀብት ትግበራ የልቀት መጠኑን ወደ 9.5 ሚ.ሜ.ቶን ሲቀንሰው ይህም በተለመደው አሰራር በ2022 ዓ.ም ከሚኖረው ልቀት ጋር ሲነፃፀር የ17.1% (-2.0 ሚ.ሜ.ቶን) ቅነሳ አለው።

4.6. የኢንዱስትሪ ዘርፍ

የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ድርሻ ባለፉት ቅርብ ጊዜያት ውስጥ እያደገ የመጣ ሲሆን የ10-ዓመት ዕቅድ ላይ ደግሞ ዘርፉ ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት (GDP) ያለው ድርሻ በ2022 ዓ.ም 17.2% እንደሚደርስ አስቀምጧል። ይህም በቀጣይ ዓመታት ከዘርፉ የሚወጣውን ልቀት እንዲጨምር ያደርገዋል።. ለዚህም የልቀት መጠኑን በቀጣይ ዓመታት ለመቀነስ የሚያስችሉ ሁነኛ ተግባራት ተለይተዋል። እነዚህም ተግባራት በለጋሽ ሀገራትና በሀገር ውስጥ ሀብት ድምር የልቀት መጠኑን በ2022 ዓ.ም 22.6 ሚ.ሜ.ቶን እንዲደርስ የሚያስችሉ ሲሆን በተለመደው አሰራር በ2022 ዓ.ም ከሚኖረው ልቀት ጋር ሲነፃፀር የ13.4% (-3.5 ሚ.ሜ.ቶን)

ቅነሳ ይኖረዋል። በሀገር ውስጥ በሚመደብ ሀብት ትግበራ ደግሞ የ27.3 ሚ.ሜ.ቶን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ይመዘገባል።.

በኢትዮጵያ የሚገኙት አብዛኛዎቹ ኢንደስትሪዎች ታዳጊ በመሆናቸው ከፍተኛ የሆነ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት የላቸውም። የሲሚንቶ ምርት ዘርፍ ከምርት ሂደት ጋር ተያያዥነት ስላለው ዋና የዘርፉ የልቀት ምንጭ ነው። ከዚህ ሁኔታ በተለየ ኢትዮጵያ በሚቀጥሉት ዓመታት ማዳበሪያ ለማምረት ያቀደች ሲሆን ይህም የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት እንዲጨምር ያደርገዋል:: በዚህም መሰረት በሲሚንቶ ኢንደስትሪ ዋና የማስተሰሪያ ፖሊሲ ክሊንከርን መተካት ነው። ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ መጠቀምን መቀነስ ከዘርፉ የሚኖረውን ልቀት ለመቀነስ አንዱ የማስተሰረያ ስትራቴጂ ነው።

4.7. የሰብል ምርት ዘርፍ

ከሠብል ምርት ዘርፍ ለሚወጣው ልቀት ምንጩ የማዳበሪያ አጠቃቀም፣ የሰብል ተረፈ ምርት፣ የእንስሳት ሽንትና ፍግ ጋር ይየያዛል። በዚህም ምክንያት ዘርፉ አብዛኛውን የዘርፉን ተግባራት በፖሊሲ ለይቶ ካስቀመጣቸው የእንሰሳት ዘርፍ ጋር የቀጥታ ግንኙነት አለው። ይህንን ዘርፍ ለብቻው ለይቶ ማስቀመጥ ያስፈለገበት ምክንያት የእንሰሳት እርባታና ሰብል አመራረትን ለመለየትና ከመንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ትግበራዎች መመሪያ ጋር ለማጣጣም ነው። በ2022 ዓ.ም በተለመደው አሰራር ከእንሰሳት ዘርፍ የሚመነጨው ልቀት መጠን 48% የተገመተ ሲሆን ይህም ከጠቅላላ የልቀት መጠን 3% ድርሻ ይኖረዋል።

5. በተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ተግባራት አስተዋፅኦ

ኢትዮጵያ ባለፉት አስርት ዓመታት ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ተግባራትን ስታከናውን ቆይታለች። ዋና ዋና የፖሊሲና መዋቅራዊ እርምጃዎች ሲተገበሩ የቆዩት ሀገራዊና የዘርፍ የልማት ዕቅድ ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያን በማካተት እና በተመረጡ ዘርፎች ውስጥ የተለዩ የማጣጣሚያ አማራጮችን መተግበር ላይ ትኩረት በመስጠት ነው።

አደገኛ ጉዳት እያደረሰ ያለውን የአየር ንብረት ለውጥና እንደ ድርቅና ጎርፍ የመሳሰሉትን አደጋዎች በሚያጠቃልለው የአየር ንብረት ሁኔታ ተለዋዋጭነት ምክንያት የሚስተዋለውን ተጋላጭነትና ተፅዕኖውን የመቋቋም ዝቅተኛ ችሎታን ከግንዛቤ በማስገባት፣ መንግስት ለአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ትግበራ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል። በዚህ አውድ ውስጥ ውጤታማና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ ያለንን አነስተኛ ሀገራዊ ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የማጣጣሚያ ተግባራት መለየት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ምንም እንኳ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ በበቂ ሁኔታ የማጣጣሚያ ተግባራት ያላካተተ ቢሆንም በርካታ ዘርፎች የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን የመቋቋም ችሎታን ለመገንባትና ተጋላጭነትን መቀነስ ላይ ያለው ትኩረት እያደገ በመምጣቱ አስፈላጊነቱን አረጋግጠዋል። በ2009 ዓ.ም የግብርና፣ የደን፣ የጤና፣

የትራንስፖርት፣ የኢነርጂ፣ የኢንደስትሪ፣.የውሀና የከተማ ልማት ዘርፎችን ባካተተ መልኩ ሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድ መውጣቱም ለዚህ ስራ የተሰጠውን ትኩረት ያሳያል። በተጨማሪም ሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድ የትግበራ ፍኖተ-ካርታ የማጣጣሚያ ዕቅዱ ላይ የተለዩትን ዘዴዎች በማስፋት በአጭር-ዘመን (2012-2014 ዓ.ም) የሚተገበሩ የአቅም ግንባታ፣ ምቹ ሁኔታን መፍጠርና ምርምርን ማጠናከር ያሉ ድርጊቶችን ለመተግበር ያለመ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ ዘርፍ ተኮር በሆነ መልኩ የረጅም-ዘመን ተግባራትን ከ2017-2022 ዓ.ም ለመተግበር ታቅዷል።

ሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድ የትግበራ ፍኖተ-ካርታ ከተለዩት የረጅም-ዘመን ተግባራት ላይ በመጨመር በተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ውስጥ መካተት ያለባቸው 40 ተግባራት ተመርጠዋል። በሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅዱ ላይ የተለዩት 18 ማጣጣሚያዎችና በዕቅድ የትግበራ ፍኖተ-ካርታ የተለዩት ተግባራት የባለድርሻ አካላት ባሳተፈ ሁኔታ ተከናውኗል።

ተገቢ የሆኑትን ተግባራት ከማጣጣሚያ ዕቅዱና ፍኖተ ካርታው ውስጥ ለመለየት የመምረጫ መስፈርትም ተቀምጧል። በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ የሆነው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ የፋይናንስ፣ የማህበራዊ፣ የቴክኖሎጂ፣ የህግና የአካባቢ ክፍሎች ትንተና (PESTLE analysis) በእያንዳንዳቸው ስር አራት መስፈርቶች በማስቀመጥ ተከናውኗል።

የተለዩ የማጣጣሚያ ተግባራት


ኢትዮጵያ ቁርጠኝነቷን ያሳየችባቸው የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ተግባራት በግብርና፣ የመሬት አጠቃቀምና ደን ላይ በዋናነት ያተኮሩ ሲሆን ከነዚህ በተጨማሪም የውሀ፣ የጤና፣ የኢነርጂ፣ የትራንስፖርትና የከተማ ልማት ዘርፎች ይገኛሉ።

አስፈላጊ የሆኑ የማጣጣሚያ ተግባራትን በእነዚህ ዘርፎች ውስጥ እየተከናወኑ የቆዩ ሲሆን ለወደፊትም ከአየር ንብረት ጋር የተጣጣመ ግብርና፣ የእንሰሳት እርባታ ብዝሀነት፣ ድርቅን መቋቋም የሚያስችል የእንሰሳት እርባታ ቴክኒክ፣ የተሻሻለ የግጦሽ መሬት አስተዳደር፣ የተሻሻለና ድርቅን መቋቋም የሚችል የሰብል ዝርያ፣ የሰብልና የእንሰሳት ኢንሹራንስ አገልግሎት፣ የተፋሰስ አስተዳደርና ልማት፣ ስነ-ምህዳርን መሰረት ያደረገ የማጣጣሚያ ስራ፣ ዘላቂ የደን አስተዳደር፣ ማህበረሰብ ተኮር የደን አስተዳደርና የደን ልማትና መልሶ ማገገም ያሉ ተግባራትን ለማከናወን ታቅዷል። ከእነዚህ ጥረቶች የሚገኙ ጠቀሜታዎችን በፍትሀዊነት ለመጠቀም ስርዓተ ፆታን መሰረት ያደረገ ሂደት በሁሉም ተግባራት ጥቅም ላይ ይውላል። ከእነዚህ ተግባራት ጎን ለጎንም ማህበረሰቡ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ መቋቋም የሚያስችል የኑሮ ዘዴ አማራጮችን ለማስፋፋትም ጥረት ይደረጋል።

የተሻሻለው በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ከሀገር ውስጥና ከለጋሽ ሀገራት በሚገኝ ሀብት የሚከናወኑ ተግባራትን በመለየትና የግብርና፣ የደን፣ የውሀ፣ የትራንስፖርት፣ የከተማ፣ የጤና፣ የመሬት አጠቃቀም፣ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም፣የአየር ንብረት አገልግሎት እና የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዘርፎችን የሚሸፍኑ 40 የማጣጣሚያ ተግባራትን ለይቷል።

እነዚህ አማራጮችም የማጣጣሚያና የማስተሰሪያ እንዲሁም ሁለቱን አማራጮች በጥምረት የሚያሳኩ ናቸው። በተጨማሪም ተሻሽሎ የተዘጋጀው በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ለእያንዳንዱ የማጣጣሚያ አማራጮች የ2010 ዓ.ም መነሻ-መረጃ እና 2022 ዓ.ም ሚላማ ለእያንዳንዱ የማጣጣሚያ ግቦች ተቀምጧል። በተጨማሪም የዕቅዱን አፈፃፀም የሚመራ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ፣ የስርዓተ ፆታና ሌሎች ባለ ብዙ-ዘርፍ ስራዎች በበቂ ደረጃ ተለይተው ተካተዋል።

የግብርና፣ የደን እና የሌሎች የመሬት አጠቃቀም ዘርፎች ውስጥ የተለዩት የማጣጣሚያ አማራጮች በሌሎች ዘርፎች ማለትም ውሃ፣ ኃይል፣ ትራንስፖርት ፣ የከተማ ልማት፣ ጤና፣ እና የአደጋ ስጋት ቅነሳ የሚያጠቃልሉ ናቸው።




ምስል 5- በየዘርፎቹ የሚተገበሩ የማጣጣሚያ አማራጮች

6. የማስተሰርያ ልኬት፣ዘገባና ማረጋገጫ እና የማጣጣሚያ ክትትልና ግምገማ

የተሻሻለው ዕቅድ የልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጫ እና የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ በትግበራ ላይ ያለውን የፓሪስ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ማዕቀፍ ላይ ከተቀመጡት አንቀጾች ማለትም አንቀፅ 4 (ማስተሰርያ)፤ አንቀፅ 6 (የትብብርን አቀራረብ) ፤ አንቀፅ 7 (ማጣጣሚያ)፤ እና አንቀፅ 13 (የተሻሻለ የግልፀኝነት ማዕቀፍ) ጋር በተናበበ መልኩ የተዘጋጀ ነው። አንቀፅ 13 ሀገራት በዓመት ሁለት ጊዜ ዘገባ የሚያቀርቡባቸውን ዝርዝር ጉዳዮች የያዘ ሲሆን እንደ ኢትዮጵያ ያሉና በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሀገራት የሙቀት አማቂ ጋዞች ቅነሳ ዘገባቸውን እንደ ሀገራቱ ፍላጎት ማቅረብ እንደሚችሉ ያስቀምጣል።

ሀገራችንም ይህን የተሻሻለ ዕቅድ በማቀድ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ ዝግጅትና ትግበራ ተምሳሌትነቷን ለማስቀጠል በቁርጠኛነት በመተግበር ላይ ትገኛለች። በመሆኑም በግዴታ ላይ የተመሠረተ የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ዘገባ፣ በአግባቡ ተመዝግቦ የተያዘ የካርበን ግብይት መረጃ ስርዐት እና ዘላቂ ልማትን በተመለከተ የመረጃ ልውውጥ እና በአካባቢ ጉዳዮች ላይ መተማመንና ግልፅነት እንዲኖር በቁርጠኝነት ትሰራለች። ይህንንም ለማሳካትም የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ የክትትል፣ ዘገባና ማረጋገጫ ስርዐት በሁሉም ዘርፎች ከ10 ዓመት የልማት ዕቅድ ከአመላካቾች ጋር ተመጋጋቢ እንዲሆኑ ተደርጓል። ስለዚህ የልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጫ ማዕቀፍና የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ለዕቅዱ ትግበራና ለተ.መ.ድ የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት ሴክሬታሪየት፣ለአጋር አካላት እና ለዓለምአቀፍ ማህበረሰብ ሪፖርት ማድረግ በሚያስችል መልክ

ተዘጋጅቷል። በተጨማሪም ዕቅዱ ለጋሽ አካላት በቴክኖሎጂ በመደገፍ ማግኘት እንዲችሉ መረጃዎችን ካሉበት ሆነው የሚሰበስቡበት እና የሚዘግቡበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የአቅም ግንበታ ስራን ከግምት ውሥጥ ያስገባ ነው ።



ምስል 6፤ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ ላይ ያተኮሩ የልኬት፣ ዘገባና ማረጋጫና የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ

7. ለዕቅዱ ትግበራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

7.1 በሀገር ውስጥ የሚሸፈኑና ከአጋር አካላት መሰብሰብ ያለባቸው የፋይናንስ ፍላጎቶች


ከታች በምስል 4 ላይ እንደሚታየው በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ውስጥ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድን ለመተግበር የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠን 316 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ይገመታል። በዕቅዱ ውስጥ ለተለዩ የማስተሰሪያ አማራጮች ትግበራ 275.5 ቢሊዮን ዶላር የሚያስፈልግ ሲሆን የማጣጣሚያ እርምጃዎች ትግበራ ደግሞ 40.5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ያስፈልጋል። የፋይናንስ ፍላጎቶች የተገመቱት ከዘርፎች የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖዎችን ለመቋቋም ከተዘጋጁ የማጣጣሚያ ዕቅዶች እና በ2022 ዓ.ም ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት ካለሙው የኢትዮጵያ የአስር ዓመት የልማት ዕቅድ ነው።



ምስል 7 ፣ የተሻሻለውን የኢትዮጵያን በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ለመተግበር የሚያስፈልግ ፋይናንስ

ከጠቅላላው በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ የፋይናንስ ፍላጎት ውስጥ 20% የሚሆነው በሀገር ውስጥ የሚሸፈን ሲሆን 80%

የሚሆነው ደግሞ በአጋር ሀገራትና ድርጅቶች በሚገኝ ድጋፍ የሚሸፈን ይሆናል። ይህም ማለት ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ ማስተሰሪያና ማጣጣሚያ እርምጃዎች ከሀገር ውስጥ ሀብቷ 63.2 ቢሊዮን ዶላር ኢንቨስት እንደምታደርግ ይጠበቃል። ይህም ሀገሪቱ እስከ 2022 ዓ.ም ድረስ በአማካይ በዓመት 6.32 ቢሊዮን ዶላር ኢንቨስት እንደምታደርግ የሚጠበቅ ይሆናል ማለት ነው። የተቀረው 252.8 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ፋይናንስ በአንፃሩ ከዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ፋይናንስ ምንጮች እንደሚገኝ ይጠበቃል (ምስል 5ን ይመልከቱ) ።



ምስል 8- በሀገር ውስጥና ከአጋር ሀገራትና ድርጅቶች የሚመነጭ የፋይናንስ ድርሻ

7.2 የአቅም ግንባታ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር

ከአየር ንብረት ፋይናንስ ባሻገር በኢትዮጵያ የተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ላይ የተቀመጠውን ዕቅድ ለማሳካት ተመጣጣኝ የአቅም ግንባታ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ያስፈልጋል። ኢትዮጵያ በተለይም በደን፣ በግብርና፣ በኢነርጂ፣ በኢንዱስትሪ እና በአደጋ ስጋት ቅነሳ ላይ ልዩ ትኩረት በማድረግ በተለያዩ ዘርፎች በማጣጣሚያና እና በማስተሰሪያ አማራጮች ቁርጠኝነቷን የሚያሳይ የተለጠጠ ዕቅድ አስቀምጣለች።

ኢትዮጵያ በተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅዷ ውስጥ የተለዩትን የማስተሰሪያና የማጣጣሚያ አማራጮች ሙሉ በሙሉ ለመተግበር በሚከተሉት መስኮች የአቅም ግንባታ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ድጋፍ ያስፈልጋታል።

- የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳን ልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጫ ስርዓት እና ተቋማዊ አደረጃጀቱን በበቂ መሠረተ ልማት እና በሰው ኃይል ማጠናከር፤ ይህም በቂ ክህሎት እና ዕውቀት ያለው ባለሙያ ማሟላትን እና የተቋም አቅምን መገንባትን የሚጠይቅ ሲሆን ይህ የዕቅዱን የአፈፃፀም ሂደት ለመከታተል እና ወቅታዊ ሪፖርቶችን ለማዘጋጀት የሚረዳ ይሆናል፤
- ለአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ለመስጠት የሚመደበውን የበጀት ምደባ እና ፍሰት ለማወቅ የሚረዱ በሁሉም የመንግስት ተቋማት ላይ የወጪ ግምገማ ማዕቀፍ መዘርጋት፤
- የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ልኬት፣ ዘገባ ማረጋገጫ እና የክትትልና ግምገማ ስርዐትን ከአጠቃላይ ብሔራዊ ስታቲስቲካዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ጋር ማቀናጀት፤
- ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የመረጃ ተደራሽነትን እና አቅርቦትን ማሻሻል፤
- የተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ የአፈፃፀም፣ የክትትል እና ግምገማ ስርዐት መኖሩን ለማረጋገጥ በዘርፎች እና በክልሎች መካከል ያለውን ቅንጅት ማጠናከር፤
- ንፁህ የስሚንቶ አመራረት፣ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓት፣ የተፋሰስ እና ዘላቂ የመሬት አጠቃቀም አያያዝን የሚያፋጥን የቴክኖሎጂ ሽግግር ስርዐት መዘርጋት ናቸው።

7.3. የፖሊሲ ስልቶች እና ተቋማዊ አደረጃጀቶች

7.3.1. የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገርና አረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት የኢትዮጵያ የ10 ዓመት ዕቅድ ስትራቴጂያዊ ምሰሶዎች አንዱ ነው። ሀገሪቱ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት ያላትን ቁርጠኝነት ሌላው ማሳያው የማስተሰርያና የማጣጣሚያ አመላካቾች በዘርፋዊ ቁልፍ የስኬት አመላካቾች ውስጥ መካተታቸው ነው። እቅዱ እንደነዚህ ያሉ የአየር ንብረት ለውጥ ቁልፍ የአፈጻጸም ስኬት አመላካቾች ማካተቱ ደግሞ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ አለው። በተለይም አመላካቾቹ የተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ የሚወሰዱ እርምጃዎችን አፈፃፀም ከመከታተል በተጨማሪ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ የተወሰዱ እርምጃዎችን የተመለከቱ መረጃዎች አደራጅቶ ለመያዝ የሚረዳ የመረጃ ቋት ለማበልፀግ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ምክንያቱም ብዙ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ እርምጃዎች አመላካቾችን በዕቅድ ማካተት ዘርፎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የዕቅዱን አፈፃፀምና የአፈፃፀሙን ሂደት ለመከታተል ተጨማሪ መረጃ እንዲያገኙ የሚያስችልና የመነሻ መረጃ ለቀጣይ ስራዎች ስለሚያስፈልግ ነው። የተደራጀ የመረጃ ቋት መገንባቱ ለሀገሪቱ የተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተውን የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ አፈፃፀም እና ሌሎች እቅዶች በበቂና ተጨባጭ መረጃ ላይ እንዲመሰረት ይረዳል። ይህም ራሱን የቻለ ግን ደግሞ የተናበበ እና ጥብቅ የአፈፃፀም መለኪያ እና የሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት እንዲኖር ይረዳል። በተጨማሪም የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ለመስጠት የሚረዳ የፋይናንስ ፍሰት እንዲኖር የሚረዳ ትክክለኛ የሪፖርት ስርጭት እንዲኖር ያስችላል።

በተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተውን የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ የተለዩ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ እርምጃዎች እንዲሁም ሌሎች ለአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ መቀነስ የጋራ ጥቅም ያላቸው የግብ መለኪያ መነሻዎችንና ግቦችን የሚያካትቱ ናቸው። ይህም የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት ለመቀነስ እንዲሁም በሁሉም የመንግስት ልማት ፕሮግራሞች ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን ለመቀነስ ቀጣይ እርምጃዎችን ለመውሠድ እድል ይሠጣል።

7.3.2. ከግሉ ዘርፍ ጋር መሥራት

በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ተቋም ስር የተደራጀው ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት ፋሲሊቲ የግሉ ዘርፍ በሀብት ማሰባሰብ እንዲሁም የተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተውን የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ትግበራ ውስጥ ለቴክኒካዊ አጋርነት የነቃ ተሳትፎን ለማረጋገጥ የግሉ ዘርፍ አገናኝ ቢሮ (ወይም ባለሙያ) የሚያቋቁም ይሆናል። ይህም ተልእኮውንና ተግባራቱን በይፋ በመለየት ወደ ሥራ የሚገባ ይሆናል።

7.4. የካርቦን ግብይት

ኢትዮጵያ በፓሪስ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት በኩል ከሚገኙ የካርቦን ግብይት ዕድሎችን ለመጠቀም ከፍተኛ ፍላጎት አላት። የኢትዮጵያ የመጀመሪያው የተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተውን የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ውስጥ እንደተመላከተው ሀገሪቱ በፓሪሱ ስምምነት የሚታገዘውና የካርበን ግብይትን በሚመለከቱ የአካባቢ ጉዳይ አካታችነትን፣ ተጠያቂነት እና ዘላቂ ልማት ማስፋፋት ላይ የተመረኮዘ የካርቦን ግብይት ላይ ለመሳተፍ ፍላጎት እንዳላት አመላክቷል። ኢትዮጵያ

ጉዳዩ በሚመለከታቸውና የካርቦን ግብይት ተነሳሽነት ካላቸው እንደ ኪዮቶ ፕሮቶኮል፣ ንፁህ የልማት ስልት (ሲዲኤም)፣ የፈቃደኝነት የካርቦን ደረጃዎች እንዲሁም በማደግ ላይ ያሉ የባለብዙ ወገን እና የሁለትዮሽ አካሄዶች በመሳተፍ ልምድ ያገኘች ሲሆን በተጨማሪም የአገር ውስጥ የካርቦን ገበያ ለማልማት ትፈልጋለች። ሆኖም ሀገሪቱ ለሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት ቅነሳ ካላት አቅምና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኦኮኖሚ ስልትም ሆነ የተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ላይ ከተቀመጠው የተለጠጠ ዕቅድ አንፃር ሀገሪቱ የካርቦን የግብይት ዘዴዎችን በማስተናገድ ረገድ ውጤታማ አልሆነችም።

በመሆኑም ኢትዮጵያ በፓሪሱ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት አንቀጽ 6 በሚተዳደሩና በመዘጋጀት ላይ ያሉ ዓለም አቀፍ የካርቦን ግብይቶች ላይ በመሳተፍ ይህንን ሰፊ ክፍተት ለመቅረፍ አስባለች። ኢትዮጵያ የካርቦን ግብይትን እንደ መልካም እድል በመጠቀም የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ለመስጠት ፍላጎቷን በማሳደግ በአካባቢ ጥበቃ በምትሰራቸው አስተማማኝ ስራዎች፣ በሰፋፊ የቆጠራ ስርዓት ምስረታ እንዲሁም ዘላቂ ልማት በማስፋፋት ላይ በትኩረት ትሰራለች። ይህንንም ፍላጎት ለማሳካት የኢትዮጵያን የካርቦን ግብይት የገበያ ዕድሎች የማልማት አካል በመሆን የሚከተሉት ተግባራት የሚከናወኑ ይሆናል።

- በተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ውስጥ የተለዩና ቅድሚያ በተሰጣቸው ዘርፎች የሚተገበሩና የሀገር ውስጥ እና ዓለም አቀፍ ድጋፎችን የመሳብ አቅም ያላቸው ተጨማሪ የአየር ንብረት ለውጥ ስርየት አቅሞችን መለየት፤

- ፍላጎት ካላቸው የተለያዩ አካላት ጋር መተባበርና በሁለትዮሽ ስምምነቶች ላይ በንቃት መስራት እንዲሁም በአዳዲስ የባለ ብዙ ዘርፋዊ ስልቶችና ዘዴዎች ውስጥ መሳተፍ፤
- የፓሪስ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት መስፈርቶች ማሟላት ይቻል ዘንድ ተቋማዊ አቅምን መገንባት፣ መመሪያዎችን ማሻሻልና ስምምነቱን ለመተግበር የሚያግዙ ግብዓቶችን በማሟላት የስምምነቱን ዝርዝር የማስፈፀሚያ ሰነድ፣ የልኬትና የዘገባ አቀራረብ መስፈርቶችን ማሟላት፤
- ዘመናዊ የመረጃ ቋት መገንባትን፣ በፓሪሱ ስምምነት አንቀጽ 6 የትብብር ድንጋጌ መሠረት የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት እንዲሁም የሚከናወኑ ተግባራትን በጥራት ለማፅደቅ የሚረዳ መመሪያ ማዘጋጀት፣ የዓለም አቀፍ ተሸጋጋሪ የስርየት ውጤቶች (ITMO) ዝውውር ማረጋገጥና መፍቀድ፣ የካርቦን ዋጋን ለመተግበር እና የአንቀጽ 6 የሪፖርት ኃላፊነቶችን ለመወጣት የአሠራር ሂደቶችን መዘርጋት፤
- ከፓሪሱ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት ባሻገር እንደ የዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት (ICAO's) እና ሌሎች ተጨማሪ የካርቦን ግብይት መሣሪያዎችን የዕቅዱን ትግበራ ለመደገፍ ያላቸውን እምቅ አቅም መዳሰስ፤
- የካርቦን ግብይትና የአየር ንብረት ፋይናንስን ለማንቀሳቀስ ዝግጁነትን በመገንባት ሂደት የእርስ በእርስ ትምህርቶችን እና መልካም ልምዶችን ለመለዋወጥ የሚያስችሉ ተሳትፎዎችን ማድረግ የሚሉት ናቸው።

ማ ጠ ቃ ለ ያ

የኢትዮጵያ የተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተውን የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ ከዚህ ቀደም የተከናወኑ የአየር ንብረት ለውጥ የፖሊሲ እርምጃዎች እና የአተገባበር ልምዶች፣ በተ.መ.ድ. ማዕቀፍ ውስጥ ስምምነት የተደረሰባቸውን ጉዳዮች እንዲሁም የሀገሪቱን ስትራቴጂያዊ የልማት እቅዶች ታሳቢ ባደረገ መልኩ የተዘጋጀ ነው። እቅዱ ከሚመለከታቸው ባድርሻ አካላት ምክክር በማድረግ የተለዩ የስርየትና የማጣጣሚያ አማራጮችንና ለትግበራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች የሚገኙበትን ስልት ያመላከተ ነው። ከዚህ በተጨማሪም የትግበራ ሂደቱን ለመለካት፣ ለመዘገብና ለማረጋገጥ እንዲሁም ለመከታተልና ለመገምገም የሚረዳ የአሠራር ሥርዓት በሚያመላክት መልኩ የተቀረፀ ነው።

የኢትዮጵያ የተሻሻለው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተውን የአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ዕቅድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ባሉ መስፈርቶች ሲታይ የተለጠጠና በፓሪሱ የአየር ንብረት ለውጥ የተቀመጠውን ግብ የሚያሳካ ነው።

የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖዎች መከላከያ እርምጃዎች ማሻሻያ ፕሮግራም (The Climate Action Enhancement Package (CAEP)) ለዚህ ሰነድ መዘጋጀት እና ለህትመት መብቃት አስተዋፅኦ አድርጓል። በሰነዱ ውስጥ የተገለፁ አመለካከቶች የለጋሾችን ወይም CAEP ን የሚያስተዳድሩ አካላትን አይወክልም።

ይህ ሥራ የተከናወነው ከኔዘርላንድስ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከካናዳ ዓለም አቀፍ የልማት ምርምር ማዕከል በተገኘ ድጋፍ፣ የአየር ንብረት ለውጥ ልማትና የእውቀት መረብ (Climate and Development Knowledge Network (CDKN)) ፕሮግራም አካል በመሆን ነው። በሰነዱ ውስጥ የተገለፁት አስተያየቶች የኔዘርላንድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን ወይም የዓለም አቀፍ ልማት ምርምር ማዕከሉን ወይም የአስተዳደር ቦርዱን ወይም CDKN ን የሚያስተዳድሩትን አካላት አይወክልም።